# የበእውቀቱ ስዩም የተስፋዬ ገብረአብና የእኛ ኢትዮጵያ

(ዮሴፍ ወርቁ ደግፌ)

«ነፍጠኞች የሴቶቻችንን ጡት እኛ ከበግ ላይ ጸጉር እንደምንሸልተው እንዲያ ነበር የሚቆርጡት። እነዚህ ሰዎች በግ ሲያርዱ በስመአብ ብለው ይጀምራሉ። የሴቶቻችንን ጡት ሲቆርጡ ግን በስመአብ አይሉም። ግን ሀይማኖት አለን ይሉናል»

(ተስፋዬ ገብረአብ "የቡርቃ ዝምታ")

«ባጠቃላይ በሚኒልክ ተፈጸመ የተባለው ያኖሌ ጡት ቆረጣ፤ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሰነዶች ላይ ያልተመሰረተ ለመሆኑ ይህ በቂ ማስረጃ ይመስለኛል። በአርሲ ታሪክ ዋና ባለሙያ የሆነው ፕሮፌሰር አባስ ገነሞ በመጽሀፉ ውስጥ ጡት ቆረጣ መፈጸሙን የሚያሳይ አንድም የታሪክ ሰነድ ማቅረብ አልቻለም»

(በእውቀቱ ስዩም "ከአሜን ባሻገር")

«በፍትህ በኩል ግን ጣሊያን ይሻል ነበር። አማራ ሲመጣ ሰው የገደለ ይገደል የሚል አዋጅ አመጡና እርስ በራስ መተላለቅ ሆነ»

(ተስፋዬ ገብረአብ "የቡርቃ ዝምታ")

«የሁላችንም አባቶች የሁላችንም ጌቶች በፈረቃ ግፍ መፈጸማቸው በታሪክ ተመዝግቧል። በዘመናችን የምሬትንና የቂም በቀል ፉከራን ርግፍ አድርገን ትተን በሚያቀራርቡ በሚያስተባብሩ ሀሳቦች ላይ ከተጠመድን ከአባቶቻችን የተሻለ አለም እንደምንፈጥር ጥርጥር የለኝም»

(በእውቀቱ ስዩም "ከአሜን ባሻገር")

የበእውቀቱ ስዩምን «ከአሜን ባሻገር» አዲስ መጽሀፍ ካነበብኩ በኋላ፥ ጥቂት ዘመናት ወደፊትና ወደኋላ በምናቤ ተንጬ ሳበቃ፥ አንድ ጓደኛዬን የበእውቀቱ ስዩምንና የተስፋዬ ገብረአብን ሥራዎች እንዴት ታነጻጽራቸዋለህ? ብዬ ጠየቅሁት። "በይዘት ነው በቅርጽ?" በማለት ጥያቄዬን በጥያቄ መለሰው። በ«ይዘት» አልኩት።

"ተስፍዬና በእውቀቱ ምንና ምን ናቸው፣
የጆሮ ጉትቻ፣ የአንገት ሀብል ናቸው"     (እንደማይል ብጠብቅም)
"ተስፍዬና በእውቀቱ ምንና ምን ናቸው፣
የመርዝና የመድሀኒት ብልቃጥ ናቸው"     (ይለኛል ብዬ ግን አልገመትኩም)

ይህች መጣጥፍ በ"መድሀኒት" እና በ"መርዝ" ብልቃጥ ሥራዎች ላይ አጭር ዳሰሳ የምታደርግ ናት። የተስፋዬ ገብረአብ እኩይ ፖለቲካዊ ትርክቶች ትዝታቸው ሳይደበዝዝ፥ ከእድሜው በላይ የበሰለው ወጣቱ ብእረኛ፣ ለመርዛማ ጽሀፎች ማረከሻ መድሀኒት፣ ታሪክን በማስረጃ እያጣቀሰ ያቀረበባት መጽሀፍ «ከአሜን ባሻገርን» ትሰኛለች።

በርግጥ ተስፋዬና በእውቀቱ በጽሁፎቻቸው ይዘቶች ብቻ ሳይሆን፥ በመጻፍ ስጦታ (natural talent) በእውቀትና በክህሎት (knowledge & skill) ደረጃም ቢሆን ሊወዳደሩ የሚችሉ አይደሉም። በእውቀቱ ስዩም ከወግ ጸሀፊነት ትልቅ ተሰጥኦ በተጨማሪ ባለቅኔ ገጣሚና፥ የታሪክ ተመራማሪ ጸሀፊ መሆኑ እየታየ ነው። ተስፋዬ ገብረአብ በቀላል ቃላት አቀራረብ ጥሩ አድርጎ የሚተርክ ጋዜጠኛና ጸሀፊ ነው። የተስፋዬ ገብረአብ ጽሁፉ ዋና ችግር የቅርጽ ሳይሆን የይዘት ችግር ነው። ተስፋዬ ገብረአብን ከበእውቀቱ ስዩም የሚለየው ነገር ከሙያ ስነምግባርና ከሞራል ሀላፊነት ውጭ፥ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ጥላቻን ወይም ጠላትነትን ማእከል አድርጎ፥ የኦሮሞን ህዝብ እንደ ፖለቲካ መሳሪያነት በመጠቀም፥ ጥናት ያላደረገበትን ፖለቲካዊ ታሪክ፥ እንደ አፈ-ታሪክ አጋኖ በመጻፍ፥ ህዝቦችን ለማጋጨት የሚጥር፥ እበላ ባይ የአስቤዛ ጸሀፊ መምሰሉ ነው።

ይሁንና በ«ጆሚላ እናት» መጽሀፉ ምርቃት ላይ፥ በዋሽንግተን ዲሲ በአንዲት ትንሽ ክፍል ውስጥ በጣም ጥቂት የኦሮሞ ልጆች ብቻ በተገኙበት ባደረገው ንግግር ላይ ተስፋዬ ምኞቱን ከዚህ በታች እንደተጠቀሰው ገልጿል። (የቪዲዮ ክሊፑም ይገኛል) መልካም ምኞት ነው።

> «በእውነቱ ቅር ነው የሚለኝ ዛሬ፥ የደስታዬ ቀን ነው አልልም። የልቤን ነው፣ የልብህን ተናገር ካላችሁኝ ደስተኛ ነኝ ልል አልችልም። ምክንያቱም የትግራይ ሰዎችም፥ ኤርትራውያንም፥ አማሮችም፥ ኦሮሞችም፥ አንድ ትልቅ አዳራሽ ውስጥ ተሰብስበው መጽሀፌን ብመርቀው ደስ ይለኛል። ይኼ ባለመሆኑ ቅር ይለኛል። ይሄ እንዲመጣ ነው የምመኘው» (የተስፋዬ ገብረአብ «የጆሚላ እናት» የመጽሀፍ ምርቃት ንግግር)

በእውቀቱ ስዩም የፖለቲካ ታሪክ ተመራማሪነቱን ፍንጭ የሚያሳይ ጠንካራ ብእር የመዘዘው እንደ ፕሮፌሰር አስመሮምና እንደ ጋዜጠኛ ተስፋዬ ገብረአብ ለመሳሰሉት፥ የኢትዮጵያ መበታተን ለኤርትራ ህልውና የሚበጅ ለሚመስላቸው፥ በጠላትነትና በጥላቻ ስሜት በተዛባ ታሪክ ለጻፉት የፕሮፓጋንዳ ስራ ምላሽ አጻፋ በመጻፍ ነው። ይህች በጥናት የተደገፈች፥ ለማጠቃሻነት (Reference) የምትበቃ ማርከሻ መድህኒት «ከአሜን ባሻገር» መጽሀፍ ናት። በእውቀቱ ስዩም ፖለቲካዊ ታሪክን ያለአድሎ (witout bias) ለመጻፍ ከእድሜው በላይ የሚታትር ብርቱ ጸሀፊ የሆነበት ምክንያት ፖለቲካዊ ወገንተኛነት ወይም ደግሞ የ«ዘሬን ያንዘርዝረኝ» የሚል የከፋ ችግር ስለሌለበት ይመስለኛል። እርሱም በተዘዋዋሪ ጠቅሶታል። በፕሮፌሰር አስምሮምና በተስፋዬ ገብረአብ መካከል ላለው ልዩነትም፥ ፕሮፌሰር አስምሮም ኤርትራ ተመልሳ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ትካለላለች ከሚል ስጋት (insecurity) ታሪክን እያወቁ፥ ነገርግን እንደሚመቻቸው እያጣመሙ የሚጽፉ ምሁር ሲሆኑ፥ ተስፋዬ ደግሞ ያለእውቀት በድፍረት፥ ያለጥናታዊ ማስረጃ አፈ-ታሪክ ላይ ተመስርቶ የሚጽፍ የአስቤዛ ጸሀፊ መሆኑን «ከአሜን ባሻገር» አብራርታለች።

የተስፋዬም ይሁን የበእውቀቱ ጽሁፎች የጸሀፊዎቹ የአስተዳደግ ተጽዕኖ የሚታይባቸው ስራዎች ናቸው።። በእውቀቱ ስዩም «አምላክ አልባ» (Atheist) መሆኑን በግልጽ እየተናገረ፥ ነገርግን በ«ከአሜን ባሻገር» መጽሀፉ «የሚያስታርቁ ብጹአን ናቸው» (ማቴ.5፥9) የሚለውን የክርስትና መርህ የሚከተል ጸሀፊ ተመስሏል። ተስፋዬ ገብረአብ ደግሞ «ክርስቲያን ነኝ» እያለ፥ ነገርግን የክርስትና መርህን ተገላቢጦሽ «በወንድማማች መካከል ጸብን የሚዘራ» (ምሳሌ 6:19) እኩይ ጸሀፊ ሆኖ ይገኛል።

በአንድ ሰው ውስጥ እንዲህ አይነት ተቃርኖ (Paradox) እንዴት ሊመጣ ይችላል? መጽሀፍቅዱስም አንድ ዛፍ ታፋጭም መራራም ፍሬ ሊያፈራ አይቻለውም ነው የሚለው። በእውቀቱ ስዩም «አምላክ የለኝም» ቢልም፥ የእምነትና የአስተዳደግ ተጽእኖ አሻራ ያረፈበት ጸሀፊ እንደሆነ ህዝቦችን በሚያቀራርቡና አድልኦ በሌለባቸው በጥናት የተደገፈ ስራዎቹ ተገልጿል። ተስፋዬ ግን የክርስትና እምነት ቢኖረውም፥ በአስተዳደጉ ኢትዮጵያን እንዲጠላ የተደረገበት ለመሆኑ፥ ማስረጃው የዘመናት የጥላቻ ምርጊት ወደጠላትነት ተቀይሮበት፥ የጽሁፍ ስራዎቹ በሙሉ ኢትዮጵያን ወደ መበታተን የሚገፋፉት መሆናቸው ነው። በርግጥ ተስፋዬ ኦሮሚያን እወዳለሁ ይላል። ኦሮሚያን መውደዱ በንጹህ ልብ ከሆነ ምንም ችግር የለበትም። ነገርግን ህዝብን በመሳሪያነት ለመጠቅምና ለእበላ-ባይነት ከሆነ፣ ጊዜውን ጠብቆ ተስፋዬ ክፉ ፍሬ የሚያፈራ ዛፍ መሆኑ አይቀርም።

ተስፋዬ ገብረአብ የአሰፋ ጫቦን የሚመስል እንደውሀ የሚፈስ ጥሩ የስነጽሁፍ ስጦታ አለው። ነገርግን በጽሁፎቹ ይዘት ምክንያት፥ ዛሬ እጅግ በጣም ጥቂት ሰዎች (ጥቂት ኦሮሞዎች ብቻ) ተወስኖ፥ ከአብዛኛው ኦሮሞም ሆነ የኢትዮጵያ ህዝቦች ተነጥሎ በቅሬታ ውስጥ እንደሚኖር በ«የጀሚላ እናት» መጽሀፍ ምርቃት ላይ ራሱ መናገሩ ከላይ ተገልጿል።

ተስፋዬ አንድን ብሄርን በከፍተኛ ጥላቻ ስሜት እያብጠለጠለ በሚጽፋቸው እኩይ ስራዎቹ በመደሰት፥ ወይም ተበቀለልን በሚል ስሌት በመጠጋት ፖለቲካዊ ድጋፍን መፈለግ፥ የራስን ትልቅ አቅም ያለመረዳትና በራስ ያለመተማመን ከፍተኛ ጉድለት ነው። ይህም ተስፋዬ ገብረአብን የኦሮሞ «መሲህ አዳኝ» አድርጎ የመቁጠር ችግር ነው። ይህንን በማለቴ "ነፍጠኛ ስለሆንክ ነው" ምናልባት የምትሉ ብትኖሩ፤ መግለጽ ካስፈለገ ከጃዋር መሀመድ የበለጠ ኦሮሞ መሆኔን ላረጋግጥ እችላለሁ። ጃዋር መሀመድ በኢሳት ቲቪ ላይ «በአባቴ 50% እስላም ኦሮሞ ነኝ በእናቴ 50% አማራ ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ነኝ» ማለቱን ያስታውሷል። ሰው ሁሉ ከአንድ ወይም ከሁለት ከሶስትም ዘር ሊወለድ መቻሉ እውነት ነው። ከዚህኛው ዘር ልወለድ ብሎ ጠይቆም አይወለድም። የሰው ትልቅነት የሚለካው ግን ለዘሩ ባለው ተቆርቋሪነት ብቻ ሳይሆን ለሰው ዘሮች ሁሉ በሚያደርገው መልካም ስራ ነው።

የበእውቀቱ ስዩም «ከአሜን ባሻገር» መጽሀፍ ይዘትዋ እንደ ርዕስዋ ነው። ወደ ሀያ በሚጠጉ አጫጭር ፖለቲካዊ ታሪኮች እና በጥቂት የወግ ጽሁፎች ተሰናስና በ246 ገጾች ተሰድራ በምጸት እያዋዛች፥ በሚስብ አቀራረብ ተዘጋጅታለች። ዋና ጭብጧም በየዘመኑ የሚሰጠንን የፖለቲካ ኪኒን ዝም ብለን አንዋጥ፤ በጋራ ላመጣነው በሽታ፥ ራሳችንን እየመረመርን፥ በመቻቻልና በመግባባት፥ መድሀኒት በጋራ እንፈልግ ነው። በእውቀቱ ስዩም በዚህች አነስተኛ መድብል ውስጥ ጠለቅ-ያለ ፖለቲካዊና ታሪካዊ ጭብጥ በማንሳት በጥናትም በመደገፍ፥ ብዥታ አለባቸው የሚላቸውን ወገኖች ፊት ለፊት በግልጽ ይሞግታል። አብዛኛዎቻችን ወደዘራችን ባጋደለ የተዛባ ታሪክ አመለካከት በመፍገምገም፤ ሚዛኑን የጠበቀ ፖለቲካዊ እይታ ለመያዝ ተቸግረናል። አካሄዳችን ልከኛ ስላልሆነ ለማንኛችንም አይበጅም። በእውነተኛ የታሪክ ማስረጃ (historical facts) ላይ ቆመን እንከራከር፥ እንግባባ፥ የወደፊቱን በማሰብ በይቅርታና በምህረት እንኑር።

ኑ ባግባቡ እንወቃቀስ፤ ማንም ከደሙ ንጹህ የለም። ሁሉም የኢትዮጵያ መሪዎች በጉልበት በግፍ የሚገዙ ነፍጠኞች ናቸው። የሩቁን ትተን ከአጼ ዮሀንስ እንኳን ብንጀምር፥ አጼ ዮሀንስ አጼ

ቴዎድሮስን ለባእድ የእንግሊዝ ጦር በር ከፍተው ለሞት አሳልፈው በመስጠት፥ ኦሮሞንም አማራንም ሁሉንም አስገብረው የገዙት በነፍጥ እንጂ በዲሞክራሲ አይደለም። አጼ ዮሀንስ ለንግስት ቪክቶሪያ በጻፉት ደብዳቤ የአዘቦ ኦሮሞ ሙስሊሞችን በሀይል መግዛታቸውን ያሰፈሩበት ማስረጃ እንዲህ ይላል።

> «ባገሬ ኧዘቦ የሚባል የኦሮሞ እስላም አለ። ከርሱም ሽፍታ ተነሳብኝ፤ ለማጥፋት ዘመትሁ፥ እነርሱንም በእግዚአብሄር ሀይል አጠፋሁኝ» (በእውቀቱ ስዩም "ከአሜን ባሻገር")

በአጼ ዮሀንስ ተባባሪነት አጼ ቴዎድሮስ በእንግሊዞች ከተወገዱ በኋላ አጼ ዮሀንስ ንጉሰ ነገስት ዘኢትዮጵያ ተብለው ጎጃምን ለማስገበር በወረሩበት ጊዜ፥ የጎጃም ባላገሮች ከአጼ ዮሀንስ ጦር እግዚአብሄር እንዲታደጋቸው ተማጽነው ኖሮ፥ እግዜር ግን ባለመድረሱ፥ ንጉሱ በጎጃም ብዙ ጦርና ህዝብ በመጨረሳቸው ከፍተኛ ሀዘን ውስጥ የወደቀች አንዲት ጎጃሜ የሚከተለውን ስንኝ ቋጥራ ነበር ይለናል «ከአሜን ባሻገር» መጽሀፍ።

> ከሀበሻ ወዲህ ከሀበሻ ወዲያ፥
> ሰውን ገረመው እኔንም ገረመኝ፤
> ዮሀንስ እግዜርን ገድሎታል መሰለኝ፤ (በእውቀቱ ስዩም "ከአሜን ባሻገር")

አጼ ሚኒልክም በ19ኛው ክፍለ ዘመን ደቡብ ኢትዮጵያ በአንድ ማእከላዊ ንጉሰ ነገስት መንግስት ስር እንዲኖር ያስገበሩት፣ በወረራ በነፍጥ እንጂ፣ በሰላማዊ መድረክ በድርድር አልነበረም። በዚያ ስልጣኔ አልባ ጭለማ ዘመን ቀርቶ ዛሬም በኢትዮጵያ ሰላማዊ ፖለቲካዊ ድርድር አይሰራም። በ19ኛው ክፍለዘመን በኢትዮጵያ ይቅርና በአውሮፓና በአሜሪካ ግዛት የተስፋፋው በወረራ በሀይል በጠብ-መንጃ ነው። በተለይም ከሚኒልክ መንግስት መስፋፋት ጋር ለሚነሳው ወቀሳ፥ የሚኒልክ ወታደር መሉ በሙሉ አማራ ብቻ በማድረግ ታሪክ ማዛባት ለማንኛችንም አይጠቅምም። የአማራ ጦር ብቻ ይሆንም ዘንድ የህዝብ ብዛት አቅም አልነበረውም። ስለዚህም በግድም በውድም (በጋብቻና በአምቻ) ከሸዋ ኦሮሞ ገዢዎችና ከጉራጌ ባላባቶች (ያካባቢ ገዢዎች) ጋር በመስማማት ከዋና ዋና የጦር አበጋዞች እንደነ ራስ ጎበና ዳጨ የመሳሰሉ የኦሮሞ ታላላቅ መሪዎችን በፊት አውራሪነት በማዝመት ሀረርን፣ አርሲን፥ ከፋን ወላይታን ሚኒልክ ማስገበር እንደቻሉ «ከአሜን ባሻገር» ማስረጃ ጠቅሳ ታብራራለች። የራስ ጎበና ልጅና የአጼ ሚኒልክ ሴት ልጅ ጋብቻ ውጤት የሆነውን የወሰንሰገድ ወዳጆን ፎቶ ማስረጃ ደግፎ ያቀረበ ታሪክ ጸሀፊ ያገኘሁት በእውቀቱ ስዩምን ብቻ ነው።

«ምኒልክ ቤተመንግስት ውስጥ ወሳኝ የነበሩ ሰዎች ከተለያየ ብሄረሰብ የተገኙ እንደሆኑ ሁሉ በማስገበር ዘመቻ የተሳተፈው ሰራዊትም እንዲሁ ኅብረብሄራዊ መሆኑ እሙን ነው። ይልቁንም ኦሮሞ ያልተሳተፍበት የሚኒልክ ዘመቻ ማግኘት ይከብዳል» (በእውቀቱ ስዩም “ከአሜን ባሻገር”)

ኦሮሞ በህዝብ ብዛትም በፖለቲካዊና በኢኮኖሚያዊ ጂኦግራፊም አብላጫ (Majority) ሆኖ ሳለ በኢትዮጵያ ፖለቲካ የመሪነት ስልጣን አልነበረውም የሚለው ዛሬም ውሀ የሚያነሳ ጥያቄ ሆኖ ይገኛል። የኢትዮጵያ መሪዎች የኦርቶዶክስ እምነታቸው ከፖለቲካ ጋር በመቀላቀል ባሳደረባቸው “በጎ ተጸእኖ” የተነሳ፥ በኦሮሞ ስማቸው በንጉስነት አልተጠሩም እንጂ ኦሮሞ ኢትዮጵያን መርቷል የሚል ወገን ብዙ ነው። ለምሳሌም የወሎው ንጉስ የሙስሊም ኦሮሞ የራስ አሊ (በኋላ በክርስትና ንጉስ ሚካኤል የተባሉት) ልጅ የሆነው ልጅ ኢያሱ እና ቀዳማዊ ሀይለ ስላሴን ይጠቀሳሉ። እንደዚሁም ከኦሮሞ ገዳ ባህል የተነሳ የኦሮሞ ንጉስ በኢትዮጵያ የነገሰ ባይኖርም በታሪክ በግልጽ እንደሚታወቀው በየጁ ዳይናስቲ (Yejju Daynasty) በ17ኛው ምዕተ አመት ኦሮሞዎች በገዳ አመራር (Collecetive Leadership) አብዛኛውን የኢትዮጵያ ክፍል የስራ ቋንቋ *ኦሮምኛ በማድረግ እንደመሩ በታሪክ ተጠቅሷል። *ኦሮምኛ በዚህ ዘመን የስራ ቋንቋ እንደነበረ አንዳንድ የውጭ ጽሁፎች ጠቅሰዋል።

በነፍጠኛነት ጉዳይም «ከአሜን ባሻገር» በታሪካዊ መረጃ ኦሮሞም ነፍጠኛ እንደነበረ ትሞግታለች። ኦሮሞ ነፍጠኛ አልነበረም ብሎ ማመን፥ ታላቁን የኦሮሞን ህዝብ ህዳጣን አድርጎ በመውሰድ፥ አሳንሶና አቃልሎ የማየት ያህል ነው። ለምሳሌ ያህል የሲዳሞ፥ የጉራጌ፥ የጌዴኦ፥ የደቡብ-ህዝቦች ነፍጠኞች የአማራ (የክርስትና) ስም ቢይዙም በርካታ ነፍጠኞች ኦሮሞዎች እንደነበሩ ወደ ቦታው ሄዶ ዛሬም ድረስ ያለውን አሻራ ለማረጋገጥ ይቻላል። እነዚም ከታላቁ ጀግና አርበኛ የሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት ሀገረ ገዥ ከነበሩት ደጃዝማች ባልቻ አባነፍሶ ጋር ባንጋችነት የሄዱት ኦሮሞዎች ናቸው። በኋላ ላይ በህዝቦች ውህደት (Assimilation) ኦሮሞነት እየቀነሰ በወቅቱ አማርኛ መናገር እንደ ስልጣኔ ወደሚቆጠርበት አማርኛ (አማራነት) መለወጥ ቀስበቀስ መጥቶ ኦሮሞውም እኔ አማራ ነኝ ማለት ጀመረ። የአሰፋ ጫቦ «የትዝታ ፈለግ» መጽሀፍም የጋሞ ነፍጠኞች ኦሮሞዎች ነበሩ ይላል።

በኢህአዴግ መንግስት፥ የጉራጌ ህዝብን ወክለው የፓርላማ አባል የበሩት ዶ/ር ጌታቸው ሀይሌ በፓርላማ ውይይት «ምን አማራ ብቻ ነፍጠኛ ትላላችሁ። የጉራጌ ነፍጠኛ እኮ ኦሮሞ ነው። ጉራጌ

መሬቱን እየለቀቀ ወደ ሌላ ኢትዮጵያ ክፍል ተሰድዶ፣ ጥሮ ግሮ ማሶ እንዲበላ የሆነው የኦሮሞ ነፍጠኞች መሬቱን ስለነጠቁት አይደለም እንዴ?» በማለት የተናገሩት በቴሌቪዥን ስርጭት መተላለፋን የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ ያስታውሳል።

ስም የመቀየር ችግር (ስም መዋጥ ይለዋል በእውቀቱ) "ከቶሎሳ ወደ ቶማስ" "ከራስ አሊ ወደ ራስ ሚካኤል" "ከተስገራ ወደ ተስፋዬ" ወዘተ የተጀመረው ከገጠሬነት ወደ ከተሜነት "መሰልጠን" እንጂ በዘር ጥላቻ ላይ አይደለም። እንዲሁም በሀይማኖታዊ በጎ ተጽእኖ በጥምቀት (በክርስትና መነሳት) ስም ነው ይለናል «ከአሜን ባሻገር» መጽሀፍ። በወቅቱ በጥምቀት ወደ ክርስትና መግባትና የክርስትና ስም መያዝ የደህንነት ብቻ ሳይሆን የመሰልጠን ምልክት ተደርጎም ይቆጠር ስለነበረ ግለሰቦች ስማቸውን እስከመቀየር ደርሰዋል እንጂ "ስምህን ቀይር" የሚል አዋጅ አልወጣም ይላል። ኦሮሞውም፥ ደቡቤውም፥ ትግሬውም (አማራውም ቢሆን እርገጣቸው፥ ድፋባቸው፥ ልዋጥህ፥ ክንዴ፥ ጌጤ፥ ብርቄ፥ ማንጠግቦሽ የመሳሰሉትን ስሞች ይዞ) "ስልጣኔ ፈልጎ" ወደ ከተሞች ሲመጣ፥ የከተሜዎች ቀልድ እያስጠላው ስሙን ቀየረ እንጂ ዘርን የማጥላላት ጉዳይ አልነበረም። የተስፋዬ ገብረአብ «ጫልቱ እንደ ሄለን» የተጋነነ ትረካ ዋጋ የሚያጣውም ለዚህ ነው።

የዘር ማንዘር ጉዳይ በተለይም የመሪዎቻችን ከተነሳ፥ ለምሳሌ ሀይለ ስላሴ ከኦሮሞነት ወደ አማራነት ራሳቸውን የቀየሩ ንጉስነገስት ናቸው። እናታቸው ከጉራጌ የተገኘች ቆንጆ ሴት፤ አባታቸውም ራስ መኮንን ጉዲሳ ኦሮሞ ናቸው። የሀይለስላሴ ባለቤት እቴጌ መነንም የወሎው ሙስሊም ኦሮሞ ንጉስ አሊ (በኋላ ንጉስ ሚካኤል) የልጅ ልጅ መሆናቸው ይታወቃል። አጼ ሚኒልክም አባታቸው የሸዋ አማራ፤ እናታቸው ብልህ ወላይታ ናት። መንግስቱ ሀይለማርያም ከኦሮሞ ከአማራና ከኮንሶ (ደቡብ) ብሄሮች ተወላጅ ነው። መለስ ዜናዊም ከኤርትራና ከኢትዮጵያ ወላጆች የተገኘ ነው። ኢሳይያስ አፈወርቂም ቢሆን ከኢትዮጵያና ከኤርትራ ተወላጆች የተወለደ ነው። መሪዎቻችን ከዚህና ከዚያኛው ብሄር ተወለዱ ቢባሉም በሰብዕናቸው (በሰውነታቸው) የሰሩት በጎና ክፉ ስራዎቻቸው እንጂ ዘራቸው ምንም አያደርግልንም።

«እንደው ልፉ ሲለን ነው፥ ዜግነታችን እንጂ ዘራችን አይታወቅም»

(በእውቀቱ ስዩም «ከአሜን ባሻገር»)

የአገራችን ፖለቲካዊ ታሪካችን በብዙ ሺ ዘመናት እጅግ የተሳሰረ፥ ውሉ የተወሳሰበ፥ ስንክሳር ነው። በቀዳማዊ ሀይለ ስላሴ ዘመን ብሄራዊ ጭቆና፥ በመንግስቱ ሀይለማርያም ዘመን እርስበርስ ጦርነት፥ የማይረባ የግብርና ፖሊሲ ድርቅና ርሀብ… በአሁን ሰአትም ያገሪቱ ሩብ ያህል 25 ሚሊዮን ህዝብ ከድህነት ወለል በታች፥ ከ10ሚሊዮን በላይ ህዝብ በርሀብ እየኖረ ነው። በዚህ ሂደት ከቀጠለም ለወደፊቱ የሀገሪቱ ትልቁ አደጋ በገቢ ልዩነት (Economic Inequality) ምክንያት የሚመጣ የኢኮኖሚ ጦርነት ይመስለኛል። ለደረሰብን ፖለቲካዊ፥ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች ምንጩ እኛው እንደሆንን ሁሉ፥ መፍትሄውም በሌሎች ዘንድ የማይገኝ፥ በኛው ዘንድ ብቻ የሚገኝ ነው። በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ የተጠቀሰው የአልቃሽ እንጉርጉሮ …

የገደለው ባልሽ፤
የሞተውም ልጅሽ፤
ሀዘንሽ ቅጥ አጣ፥
ከቤትሽ አልወጣ፤

ሀዘን በሀዘን ላይ ለተደራረበባት ላንዲት ሴት ብቻ የተሰናኘ ሳይሆን ለእናት ኢትዮጵያ ጭምር ነው። ለዚህም ታሪካችን ምስክር ነው። ይህ ጥልቅ ሀሳብ ያዘለ መልዕክት ከመካከላችን አንድም ንጹህ እንደሌለ ሁሉም ጥፋተኛ እንደሆነ የሚያሳይና የሚያሳስበን ነው።

በእውቀቱ ስዩም በ«ከአሜን ባሻገር» መጽሀፉ ያለፈው አለፈ ለመጭው በማሰብ በጋራ በሰላም እንኑር የሚልባት ሶስት መስመር ስንኝ እንዲህ ተቋጥራለች።

አባትህ ለገዛ፥ አያትህ ለነዳ፥
አንተ ምን አግብቶህ ትከፍላለህ እዳ፤
(ተመስገን ተካ) ይልቅ መላ ምታ፤

ማሳረጊያ፡- በዚህ ጽሁፍ አቅራቢ እምነት፥ ኢትዮጵያ እንኳን ልትበታተን ቀርቶ፥ ኤርትራም፥ ሶማሌም፥ ጅቡቲም፥ ሱዳንም፥ ሁሉም የምስራቅ አፍሪካ ቀንድ ሀገሮች፥ አንድነት በልዩነት በሚሆን (Unity with Diversity) እያንዳንዱ አካባቢውን በሚያስተዳድር የእድገት ትስስር በመጓዝ ወደ ታላቅ የምስራቅ አፍሪካ አንድ ሀገርነት መቀየር ይቻላል። ለዚህም ራእይን ባለማጥበብ መስራት ይገባል ይቻላልም ብሎ ያምናል። ነገርግን «ኢትዮጵያ ብቻ ወይም ሞት» «ኦሮሚያ ብቻ ወይም ሞት»

«ኤርትራ ብቻ ወይም ሞት» «ትግራይ ብቻ ወይም ሞት» «ኦጋዴን ብቻ ወይም ሞት» ወዘተ የሞት መፈክር ሞት እንጂ ዘላቂ ብልጽግናና ሰላም የሚያመጣ አይመስለኝም። ስለዚህ መስማማትና በጋራ መስራት የሁሉም የውዴታ ግዴታ ነው።

ዘላቂ ጥቅም እንጂ ዘላቂ ወዳጅ የለም። በኢኮኖሚ በልጦ መገኘት ብቻ ነው በግሎባላይዜሽን ዘመን የሚያዋጣው። «የሶሻሊስት ጎራ» «የካፒታሊስት ጎራ» የሚል አይዶሎጂ ቀርቷል። አሜሪካ የአለምን ህዝብ 5% ብቻ ይዛ 95% አለሙን በሞላ አንቀጥቅጣ የምትገዛበት ዋናው ሚስጢር ወታደራዊ ሳይሆን የኢኮኖሚ የበላይነት ነው። መጽሀፍ ቅዱስም «ላለው ይጨመርለታል፥ ከሌለው ያለውም ይወሰድበታል» ነው የሚለው (መንፈሳዊ ትርጉም ከአለማዊ ትርጉሙ በተቃራኒው ቢሆንም) አባይ አይገደብ የምትል ሁሉ ቆም ብለህ አስብ። የአንድ ሀገር ህዝብ የሚሆን 20 ሚሊዮን ህዝብ በርሀብ እየተሰቃየ ሳለ፣ አባይ ተገድቦ ከጣና እጥፍ ይሆናል የሚባለው የግድቡ ኩሬ ላይ አሳ በማርባት አንድ ሚሊዮን ህዝብ እንኳን ይመግባል ብሎ አለማሰብ ምን አይነት የአስተሳሰብ ልዩነት ነው? ግድቡ ባለመገደቡ ይበልጥ የሚደኸየው የሚጎዳው የኢትዮጵያ ህዝብ እንጂ ገዢው መንግስት አይደለም። የአባይ መገደብ ከከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታውም በላይ ምስራቅ አፍሪካን ከጭለማ በማውጣት በብርሀን ሀይል በማስተሳሰር ዘላቂ ሰላም የማምጣት ፖለቲካዊ ፋይዳው ግዙፍ ነው። የአፍሪካ ቀንድ ምስኪን ህዝብ ምርጫው አንድ ነው «ተባብሮ መልማት ወይም ተበታትኖ መጠፋፋት»

የእውቀትና የጥበብ እንዲሁም የኢኮኖሚ የበላይነት እንጂ የጉልበት ዘመን ላይ አይደለንም። አለምን በርግጠኛነት ሊያሸንፍ የሚችል ሀይል የፍቅር ሀይል ብቻ ነው። ለእኛም ችግር መፍትሄው ፍቅር ብቻ ነው። በጠብመንጃ የፖለቲካ ስልጣን መነጣጠቅና "በንጉስ ሀይለስላሴ መቃብር ላይ ኮ/ል መንግስቱ ሀይለማርያም" "በኮ/ል መንግስቱ ሀይለማያም መቃብር ላይ ጠሚ/ር መለስ ዜናዊ" "በ... መቃብር ላይ..." አንዱ በአንዱ መቃብር ላይ ቆሞ ስልጣን መጨበጥ መቆም አለበት። ለዚህም የአመለካከት ለውጥ ብቻ ነው የሚያስፈልገው። ይህም ከእርስበርስ ጥላቻ ነጻ በመውጣት ይጀምራል። አመለካከቱን መቃወም እንጂ ሰውየውን መጥላት መንፈሳዊም ሳይንሳዊም አሰራር አይደለም።

መጽሀፍ ቅዱስ የሚወድዱንን መልሰን መውደድ ፍቅር አይደለም ጠላቶቻችንን መውደድ እንጂ ይላል። መውደድ ቢያቅት ጠላት በአለመሆን በአለመግባባትም ቢሆን ተግባብቶ በጋራ መስራት ይቻላል። ጠላትን በመውደድ በሰላማዊ መንገድም ለማሸነፍ ሕንድን ወደ ነጻነት የመሩት ጋንዲና ጥቁር

አሜሪካዊው ፓስተር ዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ ጥሩ ሞዴል ናቸው። ማህተማ ጋንዲ እንግሊዞች በሰጡዋቸው መጽሀፍ ቅዱስ «ጠላትህን ውደድ» በሚለው መርህ ተመርተው ነው እንግሊዞችን ያሸነፉት። አለምንም ያሸነፉት። ዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግም ለጥቁር አሜሪካውያን ከባርነት ነጻ መውጣት የታገሉበት መንገድ በፍቅር ጥበብ በሰላም መንገድ ብቻ ነው። እኛስ? 2ሺ አመት ሙሉ ክርስቲያን ነን እያልን እርስበርስ መፋለም የምናቆመው መቼ ነው? የምጽአት ቀን መጥቶ እስከሚገላግለን ድረስ ነውን?

ለትምህርት የሚሰጠው ዋጋ፥ ጥሮ ግሮ በጥረት ለማግኘት የሚሰጠው ዋጋ ወድቆ፥ በአቋራጭ ሚሊዬነር እየተሆነ ነው። «ከ7 ማስትሬት አንድ የሰበታ መሬት» የሚባልበት «ህጋዊነት»ን በጠ/ሚር ሰብሳቢነት በኢትዮጵያ ቲቪ አየን። የገቢ ልዩነት (Economic Inequality) በመንግስተ ሰማይና በሲኦል የመኖር ያህል ልዩነት እያመጣ በግልጽ በሀገሪቱ እየታየ ነው። ሞራልና ስነምግባር ሀገራዊ እሴቶች እየወደቁ ሙስና (Corruption) ከላይ እስከታች በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ ሀገራዊ ባህል እየሆነ ነው። ሀገራዊ እሴቶች እንዲዳብሩ የሚሰሩ ሰዎች በጥላቻ እና በምዝበራ ለደነደነ ድንጋይ ልብ ላላቸው ሰዎችና ለተከታዮቻቸውም ጥሩ ምሳሌዎች ስለሆኑ መባዛት አለባቸው።

ለምሳሌ እንደነ ዶ/ር በላይ አበጋዝ (የህጻናት የልብ ቀዶ ጥገና ሆስፒታል ገንዘብ እያለቀሱ በመለመን ያስገነቡ) ዲ/ን ዳንኤል ክብረት (የበጎ ሰው ሽልማት /ሰዎችን በመልካም ስራቸው እውቅና መስጠት) ጎዳና የወደቁ ሰዎችን ሰብስቦ የሜቄዶኒያ አረጋውያን የመሰረተው ወጣት፤ ወዘተ የመሳሰሉት ሰዎች በጎ ጅማሬዎች መተሳሰብና የልብ አንድነት የሚያመጣ ነው። በሙዚቃ በኪነጥበብ እንደነ ቴዲ አፍሮ (“አንድ ላይ ነን ስንል ተለያይተናል”) አብዱ ኪያርንም መጥቀስ ይቻላል፤ የመሳሰሉት ለሰላም ለፍቅርና ለአንድነት አቀንቃኞች ይብዙ። ጸሀፍትና ገጣምያን እውነትን በመግለጽ ህዝቦችን ለሀገራዊ እድገትና አንድነት ማምጣት ይጻፉ፤ በእውቀቱ ስዩምም በ«ከአሜን ባሻገር» መጽሀፉ በጥሩ አቀራረብ አስታራቂ ሆኗል። የበጎ ሰዎች ተጽእኖ ከጥላቻና ወገንተኛነት የራቀ የሀገሪቱ ሞራላዊ እሴት ነው።

የእምነት መሪዎች የት ናችሁ? ከሀይማኖታዊ ፖለቲካ በመውጣት ለአዲሱ ትውልድ ሞራል እድገት መስራት የለባችሁምን? ህዝብን ለሰላምና ለፍቅር ማትጋት የለባችሁምን? ነው ወይስ ከመምህሩ ደቀመዝሙሩ የሚሻልበት የመጨረሻው ዘመን ላይ ነን? እኛን አስጨናጋፊ አላላውስ ያለን በአመለካከት ልዩነት አለመቻቻላችን (Differences by mutual concessions) ነው። እርስበርስ ጠላትነት ምክንያት

በመጠላለፍ «ውሀ ቅዳ ውሀ መልስ» (Zero-sum Political game) መጫወታችን ጎዳን። ጥላቻ ተጠይውን ብቻ ሳይሆን ጠይውንም የሚጎዳ የስሜት በሽታ ነው። ማንም በማንም ላይ ከፍቅር በስተቀር የጥላቻ እዳ ሳይኖርበት ቢሰራ ሁላችንም በሰላም እናድራለን፤ እያላችሁ መስበክና ማስተማር አለባችሁ።

በመጨረሻ የበእውቀቱ ስዩም የወግ መጣጥፎች፡- ከፖለቲካዊና ታሪካዊ መጣጥፎች በመለስ ያሉት የወግ መጣጥፎች ፈገግ እያስደረጉ በሚያስደምሙ ግላዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ትዝብቶች የተሞሉ በመሆናቸው አንባቢ ራሱን እንዲታዘብና እንዲፈትሽ የሚያደርጉ ተጽእኖ ፈጣሪዎች ናቸው። በእውቀቱ ስዩም በወግ ጽሁፎቹ ታዋቂና ተወዳጅ ከነበረው ደራሲ መስፍን ሀብተማርያም ጋር የሚተካከል ይመስለኛል። እንዲያውም እንደቀልድ እያዋዛ ከሚጽፋቸው ምጸታዊ ኮርኳሪ መልእክቶች አንጻር በእውቀቱ ስዩም ለየት ያለ ተሰጥኦ ያለው የወግ ጸሀፊ ነው። በመሪዎቻችንና በፖለቲከኞቻችን ላይም ወዝ ያላቸው፤ ክብር ነክ ያልሆኑ ወጎች የሚቀልደው በእውቀቱ ስዩም ባንድ ወቅት ጠሚ/ር መለስ ዜናዊን በተመለከተ በወግ ጨዋታ መካከል ለስልጣንም Expired Date ይኑረው ማለቱን አስታውሳለሁ። «ፖለቲካዊ ሞት ሞተዋል» የሚባሉት የምርጫ-97 ባለረጅም አፍ ፖለቲከኛ አቶ ልደቱ አያሌውን በተመለከተ የበእውቀቱ ወግ እንዲህ ትላለች።

> "የምርጫ 97 ጦስ ልደቱ አያሌውን በሄደበት ያሳድደዋል። ባንድ ወቅት ልደቱ ከጓደኛው ጋር ምሳ በልቶ ጨርሶ ወደመቀመጫው ይመለሳል። በቦታው የነበረው አንድ ተራቢ ተመጋቢ ብድግ ይልና ወደ ልደቱና ጓደኛው ቀረብ ብሎ፥ «የእጅ መታጠቢያው በየት በኩል ነው?» ይላቸዋል። ልደቱ ተሽቀዳድሞ፥ «በዚህ በኩል» ብሎ በትህትና ይጠቁመዋል። ያን ጊዜ ተራቢው፥ «አንተን አላምንህም፥ እሱን ነው የጠየቅሁት» ብሎ መለሰ"

እግዜአብሄር ማስተዋልን ይስጠን

ለትችትና አስተያየት፡- danruth2000@gmail.com